# በኢትዮጵያ ውስጥ የብሄር ተኮር የክልሎች አሸናሸንና እንደምታው

## በፖለቲካና የጥናት ኮሚቴ የተዘጋጀ

**ሐምሌ 15፣ 2009 ጁላይ 22፣ 2017)**

***መግቢያ***

የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ (ሸንጎ) የስራ አስኪአጅ ኮሚቴ የሀገራችንን ሁኔታ በየጊዜው እየገመገመ የፖለቲካ አቅጣጫ ማሳየትአንዱ ተግባሩ ነው። *ኮሚቴዉ ፌብርዋሪ 2017 ባደረገዉ ስብሰባ ዛሬ በሃገሪቱ ሰፍኖ ያለዉ ብሔር-ተኮር ፌድራሊዝም ያስከተለዉን ሃገር አቀፍ ምስቅልቅል በተለይም በቅርቡ ጎልቶ የታየዉን የወልቃይት ጠገዴን ጉዳይ ምንነት ግልፅ የሆነ ግንዛቤን ማስጨበጥ የሚችል ጥናታዊ ሰነድ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል:: በዚህም መሠረት የጥናትና ፖሊቲካ ኮሚቴ በተሰጠዉ መመሪያ ይህን አነስተኛ ጥናታዊ ፅሑፍ ሲያቀርብ* ሸንጎም ሆነ አጠቃላይ ህብረተሰቡ እንደ ተጨማሪ ግብአት ሊጠቀምበት ይችላል የሚል እምነት አለዉ::

ይህ ጥናት የአስተዳደር ክልሎች በኢትዮጵያ በተለያዩ መንግስታት ስር ምንና ምን መልክ ይዘው እንደነበር ፤ በዘመነ ህወሀት/ ኢህአዴግ የተከሰተው ብሄር ተኮር ፌዴራሊዝምና የክልሎች አፈጣጠር ርእዮታለማዊና ታሪካዊ ማእቀፉ ምን እንደሆነ ፣ ይህ ብሄር ተኮር ፌዴሊዝም ያስከተለው ችግር ምን እንደሆነ፣ ባሁኑ ሰአት ትኩረትን ስቦ የሚገኘው የወልቃይት ጠገዴና የኮንሶ ሁኔታ ከላይ ከተነሱት ርእሶች አኳያ ሲመረመር ምን እንደሚመስል የገመገመ ሲሆን በመጨረሻም የሸንጎው አባል ድርጅቶች ከላይ በተነሱት ርእሶች አኳያ የሚያመሳስላቸውንና የሚያለያያቸውን ፈልፍሎ በማውጣት ሸንጎው እንደ አንድ የድርጅቶችና የግለሰቦች ስብስብ ምን አቋም ሊከተል እንደሚገባውና ወደፊት ደግሞ በሰፊው ሀሳብ በመለዋወጥ ይበልጥ መግባባት ሊይዝባቸው የሚገባው በምን በምን ነጥቦች ላይ እንደሆነ ለይቶ አቅርቧል።
ይህን ጽሁፍ ለማዘጋጀት ሀላፊነት የተሰጠው የጥናትና ፖለቲካ ኮሚቴው ዋና ዋና የጥናት ጽሁፎችን በሰፊው ተመልክቷል።በተጫማሪም የሸንጎው አባል ድርጅቶችን ግብአት አካቷል።

*ብሔር፣ብሔረሰብ ፣ዘዉግና ጎሳ የተባሉት ቃላት ETHNIC GROUP የሚለዉን ቃል በተለዋዋጭነት ለመግለፅ ይዘወተራሉ:: ይህ ቃል በማህበረሰባዊ ተመራማሪዎች/ ባለሙያወችም ( SOCIOLOGISTS) ቢሆን ሙሉ ተቀባይነት ያለው አንድ ወጥ ትርጉም ስለሌለውበዚህ ጽሁፍ ውስጥ ብሄር/ብሄርሰብ የሚለውን ቃል ETHNIC GROUPS የሚለውን ለመግለጽ እንደተጠቀምንበት አንባቢን እናስታዉሳለን*

### የአስተዳደር ክልሎች በኢትዮጵያ

በታሪክ ውስጥ በጥንታዊነቷ ቀዳሚ ስፍራ ከሚሰጣቸው ጥቂት ሀገሮች መሀል ኢትዮጵያ አንዷ ነች። ከ3000 አመታት በላይ የመንግስት ታሪክም ያላት ሀገር ነች።

በነዚህ ረጅም አመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ ባሳለፋቸው የፍልሰት?፤ የንግድ መተሳሰር፤ በውስጥ ዝውውር (እንቅስቃሴ) በጋብቻ የመተሳሰር፣ መዋለድ፤ ድንበር አቋርጠው የመጡ ጠላቶችን በጋራ በመመከት፤ ማህበራዊ ህይወቱን በማደራጀት ሂደትና በመሳሰሉት ምክንያቶች የጋራ የሆኑ ኢትዮጵያዊ እሴቶችን ገንብቷል።

ከነዚህ እሴቶች ውስጥ ፣ (በባህል በቋንቋ በሀይማኖትና የሚታየው ብዙሀዊነት እንዳለ ሆኖ) የጋራ ታሪክና የጋራ መልክአ ምድር (ጂኦግራፊያዊ/ቴሪቶሪ) ባለቤትነቱ በአንድ ሀገር ውስጥ የሚገኝ አንድ ህዝብ መሆኑን ያረጋግጣሉ።

ከ1923 ጀምሮ ኢትዮጵያ ሁለት መንግስታት አሳልፋ አሁን ሶስተኛው ላይ ትገኛለች። በዚህ ሂደት ውስጥ ተመሳሳይነትና ልዩነት ያለው ያስተዳደር ስርአትን አስተናግዳለች።

የአጼ ቴወድሮስ መነሳት፤ ኢትዮጵያን አንድ አድርገው ለመግዛት የነበራቸው ራእይና የዘመነ መሳፍንት የማክተም ሂደት ለዘመናዊ አስተዳደር ከፍተኛ በር ከፍቷል (1855- 1868)። አጼ ቴወድሮስ ማእከላዊነትን ተግባራዊ ለማድረግ ትልቅ ጥረት ያደረጉ ሲሆን ዋነኛ የአስተዳደር ግዛቶች የአሸናሸን መሰረት ያደረጉት ደግሞ የወረሱትን የየመሳፍንቱን ግዛቶች የተከተለ ነበር።

አጼ ቴወድሮስ የተመኙትን የተማከለ አስተዳደር ተግባረዊ ለማድረግና ማእከላዊ መንግስቱን በማጠናከር ፤ቋሚና ተቀጣሪ ሰራዊትን በማቋቋም ፣ መሬት በማከፋፈል ወዘተ ሰፋ ያለ ተግባር ፈጽመዋል ።
ይህንን በመከተል አጼ ዮሀንስ 4ኛው (1872- 1889) ቀጥለውም በአጼ ሚኒሊክ 2ኛው (1889-1913) የነበሩትን የኢትዮጵያ ግዛቶች በተማከለ አስተዳደር ስር የማጠቃለል (unification) ስራ በመጠናቀቁ ዳር ድንበሯና የግዛት አንድነቷ የተረጋገጠ ኢትዮጵያን ለመቅረጽና ለማነጽ ተችሏል።

የአጼ ምኒሊክን መንግስት ተክቶ የመጣው የንጉስ ሀይለስላሴ ስርዓተ መንግስት (1923 እስከ 1966) የተዋቀረበትና ተግባራዊ ያደረገው አሀዳዊ የመንግስት ቅርጽን ሲሆን ፍጹማዊ የነገስታት (absolute monarchy) አስተዳደርም ነበር። ከፍተኛም ሆነ መካከለኛው ያስተዳደር ስልጣን በንጉሱ ደጋፊዎችና በባለሙያዎቻቸው ዝቅም ሲል በስርአቱ አገልጋዮችና ባለአደራ በሆኑ አውራ ሰወች የተያዘ ነበር። የስልጣን ምንጭም ፈላጭ ቆራጩ ንጉሱ ነበሩ።

ቀደም ሲል በተነሱት መንግስታት ጊዜ የነበረው ልምድ ቀዳማዊ ሀይለስላሴ ለተረከቧት ኢትዮጵያ ዘመናዊ አስተዳደር የማዋቀር ሂደት በግብአትነት የወረሱት አንዱ መነሻ ሀሳብ ነበር።

የንጉስ ሀይለስላሴ አገዛዝ የኢትዮጵያን ህዝብ ያስተዳድር የነበረው በአሀዳዊ የፖለቲካ ስርአት ሆኖ አገሪቱን በጠቅላይ ግዛቶች በመከፋፈል ነበር። ንጉሱ በመጀመሪያ ጥቂት የስልጣን አመታቶቻቸው ኢትዮጵያን በ32 ያስተዳደር ግዛቶች ከፋፍለው ነበር የገዙት። እነዚህ ግዛቶችም ቀደም ሲሉ የነበሩ ያካባቢ ባላባታዊ ገዥወችን ክልሎች የተከተሉ ነበሩ። ይህ በ32 ግዛቶች የተከፋፈለ አወቃቀር እስከ ጣሊያን ወረራ ቀጥሏል።

ጣልያን ኢትዮጵያን ወርሮ በያዘበት ወቅት የንጉሰ ነገስቱን 32 የአስተዳደር ግዛቶች ለቅኝ-ግዛታዊ ትልሙ አመቺ ይሆናል ብሎ ባሰበው መንገድ በብሔረሰብ ላይ በተመሰረቱ ክልሎች ተክቶ አስተዳድሯል። እነዚህም የብሔረሰብ ክልሎች አማራ ኦሮሞ እና ሲዳማ ፣ ሶማሌ፣ አዲስ አባባ እና ሐረር የሚሉት ናቸው ።

ኢትዮጽያን ወደ አስራ አራት ጠቅላይ ግዛት የተከፋፈለችው ከጣሊያን መውጣት በኋላ እና ባሌ ከሀረር፣ ተገንጥሎ ኤርትራም አንድ ተጨማሪ የኢትዮጵያ ክፍለ ሀገር ከተደረገች በሓላ ነበር። ቀደም ሲል ባሌ ከሀረር ጋር ሆኖ አንድ ግዛት ነበር።

የንጉስ ሀይለስላሴ መንግስት የኢትዮጵያ ህዝብ በ14 ጠቅላይ ግዛትና በርካታ አውራጃወች ለመከፋፈል የተጠቀመሙበት መስፈርቶች

1) ቀድመው የነበሩትን የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ዳር ድንበርና አንድነት ለማጠናከር ፤በጊዜው የነበረውን የፖለቲካ ባለስልጣኖችን ፍላጎትና አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት
2) ጂኦግራፊያዊ የሆነ የህዝብ አሰፋፈር
3) የህዝብ ብዛት
4) በስርአቱ መሪዎች ራእይ እውን ለማድረግ የተፈለገውን የተማከለ ስርአት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያግዝ አስተዳደር አወቃቀርን ግምት ውስጥ በማስገባት ነበር

የንጉስ ሀይለስላሴ መንግስት አሀዳዊ ስርአት በመሆኑ የጠቅላይ ግዛት ፓርላማና የውስጥ አስተዳደር አልነበሩትም ፤ የነበረው አንድ የተማከለ አስተዳደር ብቻ ነበር።




**የደርግና (ኢህዲሪ) አስተዳደሩ**

የ1966 አብዮትን (ሬቮሉሽን) ተከትሎ የመጣው የደርግ መንግስት የሶሻሊስት ስርአትን በኢትዮጵያ ለመገንባት በማሰብ የተመራበት የሶሻሊስት ፍልስፍና-ቅኝት (ideological orientation) ነበር። መንግስቱም የተመሰረተው (የስልጣን መጠጊያውም ሆነ መጨበጫው) ለሶሻሊስት ርእዮዓለማዊ ቅኝት ባለው ታማኝነት ነበር።

ይህ መንግስት አንድ ወጥ የሆነ ብቸኛ የፖለቲካ ፓርቲ (ኢሰፓ) ያደራጀ በመሆኑ ፣ ኢሰፓ የሀገሪቱ ፖለቲካ መሪና የስልጣን መወጣጫ ብቸኛ ማእከል ነበር።

የደርግ የመንግስት ቅርጽ አሀዳዊ ነበር። አስተዳደራዊ ክልሎች የተደራጁበት መሰረተ ሀሳብ

1. በቀድሞ መንግስታት (በሀይለስላሴ) የነበረን ታሪካዊ ልምድ በግምት ውስጥ በማስገባት ( የነበረውን እንዳለ የተቀበለበት ሁኔታ ተመልክቷል)፡

2. የህዝብ አሰፋፈርን ብዛትና የቆዳ ስፋትን
3. ለአስተዳደር የሚኖረውን አመችነት፣
4. በወቅቱ የነበረውን የሀገሪቱ የጸጥታና የአንድነት ችግሮች ግምት ውስጥ ማስገባት የመሳሰሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ነበሩ።

ደርግ በስልጣኑ የመጀመሪያ አመታት ከሀይለስላሴ የተወረሰውን የ14 ክፍለ ሀገር አስተዳደር እንዳለ ያስቀጠለ ቢሆንም ባአውሮፓውያን አቆጣጠር በ1981 አዲስ አባባን ከሸዋ ክፍለ ሀገር ነጥሎ ራሱን የቻለ አስተዳደር እንዲሆን በተጨማሪም አሰብን ደግሞ ከኤርትራ ለይቶ ራሱን የቻለ ክፍለ ሀገር በማድረግ ባጠቃላይ ሀገሪቱን በ16 ክፍለ ሀገሮች ማስተዳደር ቀጠለ።

በአውሮፓ አቆጣጠር በ1987 ደግሞ ሀገሪቱን ባዲስ መልክ በ 25 ክልሎችና 5 ራስ ገዝ አስተዳደሮች ከፋፍሎ ማስተዳደር ጀመረ።እነዚህ ራስ ገዝ አስተዳደሮች አሰብ ድሬዳዋ ኤርትራ ኦጋዴንና ትግራይ ነበሩ።የነዚህ ራስ ገዝ ክልሎች አወቃቀር በዋናነት በጊዜው የነበረውን በመሳሪያ የታጀበ ተቃውሞና የጸጥታ ሁኔታ በግምት ውስጥ ያስገባ ነበር ማለት ይቻላል።




http://www.statoids.com/uet.html
https://www.revolvy.com/topic/Provinces%20of%20Ethiopia&item_type=topic

**የኢህአዴግ (ኢፊዴሪ) ከ1983 - እስከአሁን**

የደርግን መንግስት በመጣል ስልጣን የያዘው ድርጅት መሪና መሰረት ሕወሀት ነው። ሕወሀት በትግል ላይ በነበረበት ወቅት ይከተለው የነበረው በብሄር (በብሔረሰብ) ጥያቄ ዙሪያ የመደራጀት ርእዮተ አለማዊና ፖለቲካዊ አስተሳሰብሲሆን ስልጣን ከያዘም በኋላም አጠናክሮ የቀጠለው ይህንኑ ነው።

በመሆኑም ኢትዮጵያንና ህዝቧን የሚመራበትና የሚያስተዳድርበት የፖለቲካ አመለካከትም የሚመነጨው ከዚሁ አመለካከቱ ነው።

ብሄርሰብ ተኮር አመለካከትን (Ethnicism) እንደ አይዲዮሎጂና ብሄር ተኮር ፌደራሊዝምን (ethnic federalism ) እንደ አስተዳደር ቅርጸ-መንግስትነት ተቀብሎ ተግባራዊ በማድረጉ፤ ፖለቲካም ማለትም የኢትዮጵያ ህዝብ የዜግነት ድርሻ ፤ በመንግስት ስልጣን ፤ በኢኮኖሚ ተሳትፎ ፤ ማህበራዊ ሀላፊነትን በመውሰድና የአገሪቱን ባለቤትነት የሚመለከቱ መሰረታዊ ጉዳዮችም በዚሁ በብሄር/ ብሄርሰብ ማንነትና ልዩነትን በሚያስቀድም ወይም በሚያጎላአመለካከት ማእቀፍ ውስጥ ይወድቃሉ።

ኢህአዴግ የሚከተለውና ተግባራዊ በማድረግ ላይ የሚገኘው የመንግስት አስተዳደር አይነት (system of governance) በፌዴራሊዝም ስር የሚመደብ ቢሆንም የክልሎች አወቃቀር መሰረት ያደረገው በቋንቋና በብሄረሰብ ማንነት ላይ (ethnic federalism) ነው።

ፌዴራሊዝም ባብዛኛው በዴሞካራሲያዊ ማእቀፍ (platform) ላይ የሚመሰረት የስልጣን ክፍፍል ሲሆን በማእከላዊ መንግስትና በአካባቢያዊ አስተዳደሮች መሀል የሚኖረውን የስልጣን ክፍፍል በሚዛናዊነት የሚያመቻች የመንግስታዊ አወቃቀርና አስተዳደር ያቀፈ ቅርጽ ነው። ባንጻሩ በሀገራችን ተግባራዊ የሆነው ብሄር ተኮር ፌደራሊዝም በተግባር የሚያመቻቸው ግን በመንግስት ስልጣን ላይ ሆኖ ፖለቲካውን የሚመራውን የህወሀት/ ኢህዋዴግን አምባገነን አስተዳደር ነው።

ህወሀት/ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ያሳረፈው በረጅም ታሪኩ ውስጥ ማንነቱን ባገኘው የኢትዮጵያ ህዝብ ለይ ሳይሆን ኢትዮጵያ ባቀፈቻቸው "በብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች" ላይ ነው። ይህም በሀገሪቱ ህገመንግስት አንቀጽ 8 ላይ ሰፍሮ ይገኛል። ከዚህ በተጨማሪም በአንቀጽ 39 ላይ ማናኛውም ብሄር ብሄረሰብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ድረስ መብት እንዳለው ሰፍሮ ይገኛል።

በአንቀጽ 40 ላይ እንደሰፈረው፣ የመሬት ባለቤት እያንዳንዱ ዜጋ ሳይሆን ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ናቸው። ይህ ማለት የሀገሪቱ የባለቤትነት መሰረት ዜጎች ሳይሆኑ በጥቅል ብሄር ብሄረሰቦች ናቸው ለሚለው ከፍተኛውን ድርሻ ይሰጣል።ይህ ማለትም የህወሓትን የብሔረተኛነት ዕምነትና አመለካከት በሁሉም ፖለቲካዊ ተግባሮች ላይ እንዲሰፍን እንዲገለጽናሁሉም በግድ እንዲቀበለው አድርጓል።

ስለሆነም የህወሀት/ኢህአዴግ የመንግስት አወቃቀር ከቀድሞወቹ የሀገራችን መንግስታት ያስተዳደር አወቃቀር በአይነቱም በይዘቱም ፍጹም የተለየ ነው። የሕወሀት/ኢህአዴግ መንግስት በዋናነት ቋንቋን የክልሎች ድንበር ለመከለል የተጠቀመበት መስፈርት ቢሆንም በተለያዩ አካባቢወች ደግሞ ይህንንም መመዘኛ ወደ ጎን ትቶ በወቅቱ የፖለቲካ የበላይነትን የያዙት ህወሀትና ኦነግ በፈለጉት መልክ የህዝብ ወደፈለጉት ክልል እንደመደቡ መመልከት እንችላለን።

የኢህአዴግ የክልል አስተዳደር ነባሩን የኢትዮጵያን የአስተዳደር ታሪክ፤ የጋራ ታሪክ፤ ጂኦግራፊያዊ አሰፋፈር፣ ለልማትና አስተዳደር የሚኖረውን አመችነት የተመለከተ ሳይሆን በዋናነት ብሄርንና ቋንቋን ብቻ በተናጠል መሰረት ያደረገ ፌደራሊዝም ነው።

*በዚህ መሰረታዊ ፍልስፍና መሰረት ኢትዮጵያን በዘጠኝ ብሄሮችና ቋንቋ ዙሪያ (የትግራይ፣ አማራ፣ አፋር ኦሮሚያ ቤነሻንጉል ጉምዝ ሶማሌ ደቡብኢትዮጵያ  ሀረሪ ፣ ጋምቤላ)  በመከፋፈል የክልል አስተዳደር መስርቷል።*

*ሁሉም ዋና ዋና ጉዳይ በማከላዊ ደረጃ ስልጣኑን በሚቆጣጠረው ሕወሀት/ኢህአዴግ  በሚወሰንና የክልሎች ባለስልጣኖች በነጻነት የመንቀሳቀስ ጉዳይ በተግባር የሌለ ቢሆንም እያንዳንዱ የክልል አስተዳደር " የራሱ የሆነ" ፓርላማና የክልል ፕሬዚዳንቶች ያሏቸው "መንግስታት" መስርተዋል። እያንዳንዱ የክልል መንግስት "የራሱ " የሆነ በሚኒስቴሮች የሚመራ  ያስተዳደር ተቋሞች አሉት። ከታች እስከላይ ያለው አስተዳደራዊ መዋቅርም እንደመንግስት የቀመ ያሰመሰለዋል።*




***ብሄር ተኮር ፌደራሊዝምና የክልሎች አፈጣጠር በዘመነ ህወሀት/ ኢህአዴግ***

*ባለፉት 26 ዐመታት በተለይም ህወሓት/ኢህአዴግ. በሚቆጣጠሯቸው መገናኛ ብዙሃኖች በበላይነት ሲስተጋቡየቀዩተየብሄር /የብሔረሰብ ማንነትና በዚያም ላይ የተመሠረተው የጥቅምና የሥልጣን ጉዳዮች ነበሩ።የጋራ የሆነው ኢትዮጵያዊ ማንነትና እሴቶች  እየተናደ በምትኩ ልዩነቶችን ማጉላት ዋነኛ ተግባር ተደርጎ ሲራገብ ነበር የተኖረው። ውጤቱም ዛሬ በሃገራችን እየሆነ ያለው ያ የማህበረሰቡ* ***የማንነትና  የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ*** [1]*ከምን ጊዜዉም በበለጠ  ጎልቶ የሚታይ ብሔራዊ ጉዳይ ሆኗል:: በቅርቡ በኦሮሚያ፣ በጎንደር፣ በሶማሊ፣ በወልቃይት ጠገዴ፣ በኮንሶ፣ ባአዲስ አበባና አካባቢዋ እንዲሁም በሌሎች  የሃገሪቱ ክፍሎች የተነሱ ከዚሁ ጋር የተቆራኙ ጥያቄዎችና አመጾች ጉልህ ምሳሌዎች ናቸዉ::*

*ታዲያ ይህ ሕዝባዊ የመብት ጥያቄ ከዚህ በፊት ባልታየ መልኩ በጣም ገኖ የሕዝብን ቁጣ  ሊቀሰቅስና የሃገሪቱን ብሔራዊ አንድነት ሊንድ የተቃረበ አደጋ ሊሆን እንዴት ቻለ?*

*ይህንን ሁኔታ የበለጠ መረዳት እንዲቻል በሃገራችን በሥራ ላይ የዋለዉን አዲስ የክልል አፈጣጠርና የዚህ ሌላው አካል የሆነዉን ብሔር-ተኮር ፌደራሊዝምን አመጣጥ ምንነት መመልከት ጠቃሚ ይሆናል:፡*

አስቀድመን ወደዚህ ሊያደርሰን የቻለዉን በሃገራችን ከተነሱ ዓበይት የፖለቲካ ማህበረሰብ ፍትህ (social justice) ጥያቄዎች አንዱ የሆነዉን <u>የብሔር/ብሔረሰብ ጥያቄ</u> ባጭሩ እንመልከት::

እንደሚታወቀዉ ይህ ጥያቄ ከተማሪዉ ንቅናቄ ጀምሮ ጉልህ ሥፍራን የያዘ ነዉ::
ለዚህ ጥያቄ ምላሽ " በማርክሳዊ ሌንናዊ እይታ የተቃኘ ግራ ዘመም የነበረዉ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ "የብሔሮች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል" የሚለዉን የመፍትሔ ሃሳብ ሲያስተጋባ … ከተማሪዉ አብራክ የተወለዱ ማርክሳዊ ሌንናዊ የፖሊቲካ ድርጅቶችም በምስረታቸው የመጀመሪያ አመታት (ጎልተዉ የሚታወቁት ኢሕአፓ፤ መኤሶን፣ማለሪድ ኢጭአት ወዘተ ) ይህንኑ አመለካከት ተቀበሉ:: … ወታደራዊዉ መንግሥትም የግራ ፖሊቲካን እንደ መንግሥታዊ መመሪያዉ ቢቀበልም "እስከ መገንጠል" የሚለዉን ከቶም እንደማይቀበል አስታወቀ::....

ሌሎች ብሄር ተኮር የሆኑት እንደ ኦነግ ና ሕወሃት ያሉ ድርጅቶች የብሄሮችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከ መገንጠል የሚለዉን መርህ እንደ ራሳቸዉ መመሪያ አድርገዉ ተቀበሉ:: ይህንንም ተግባራዊ ለማድረግም ታገሉ። በኋላም ኦነግንና ሌሎች ድርጅቶችን ጨምሮ በ1991 ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን ሲመጣ የአዲሱ ብሄር ተኮር ፌደራላዊ መንግሥት መሠረት ተጣለ::"* ዓለም ሃፍቱ

የግራው አመለካለት መሰረት የነበረው የተማሪወች እንቅስቃሴ በሀገራችን ውስጥ በነበሩት ስርአቶች ውስጥ ሁሉም ግለሰቦችና ማህበረሰቦች መሰረታዊ መብታቸው ተጠብቆ ዜጎች በእኩልነት የተስተናገዱበት ዴሞክራሲያዊ ስርአት ባይኖርም ፣ በሀገሪቱ ውስጥ ጭቆናን በማስወገድ፣ የመብት መከበርንና እኩልነትን ተግባራዊ በማድረግና የህዝቡንና የሀገሪቱን አንድነት በማስጠበቅ መሀል ሚዛናዊ እርምጃን ከመውሰድ ይልቅ ያመለካከት ሚዛኑ እጅግ ወደ አንድ ጎን ያጋደለ ነበር። ምንም እንኳን የነበረውን የብሄረሰብ ጭቆና በማስወገድላይ ቢያተኩርም ኅብረ-ብሔር በሆኑ ፖለቲካዊና ህዝባዊ ድርጅቶች አምካኝነት አዲስ ኢትዮጵያዊ ማንነትን የመመስረት ዓላማን አንግቦ ነበር የሚታገለው።

ከዚህ በላይ እንደተመለከተዉ የሕወሀት ታሪካዊ አነሳስ ባንድ በኩል የማርክሳዊ ሌንናዊነትን አቀንቃኝ ከነበረው የተማሪው ንቅናቄ ጋር የተያያዘ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ትግራይ በኢትዮጲያ ውስጥ የተበደለችና የተገፋች ስለሆነ የሚገባትን መብት ለመጎናጸፍ ብሄረተኛ ትግል ማካሄድ አስፈላጊ ነው ከማለት አልፎብሄረተኛነትን ርእዮትና የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል የሚለውን መር ህአንግቦ የተነሳና የተጓዘም ነው።

ሕወሀትሚዛናዊነት ባጣ መልኩ ገና ከጅምሩ ኢትዮጵያን በግዳጅ አንድ ተደርጋ እንደተያዘች ሀገር ከመቁጠር አልፎ ወደ ሀገርነት ስትመጣ ጀምሮ የብሄሮች እኩልነት ሊሰፍንባት ይችል እንደነበረ ታሪክን አድበስብሶ ያወሳል። ታሪክ እንደሚያሳየን ማንኛውም እንደ ኢትዮጵያ ያለ ኅብረ-ብሔር የሆነ ሀገር ሲመሠረት ሁሌም መሥራቾቹ ተደራድረውና ተስማምተው ወይንም እኩልነትን አስፍነው ሳይሆን በወቅቱ ሃይልና ጉልበት ያላቸው ክፍሎች በሚፈልጉት መልክና ሁኔታ ነው። የኢትዮጵያ አመሠራረትም የተለየ ሊሆን አይችልም ነበር።

ጥያቄው ያኔ በወቅቱሀገሪቱ በነበረችበት ታሪካዊ ማእቀፍ ውስጥ የነበሩትን የተዛቡ ግንኙነቶች መስተካከል አለባቸው፣ በብሔረሰቦች መሀል የመበላለጥ ግንኙነቶችም ተወግደው እኩልነት መስፈን አለበት ሊሆን ሲገባው ህወሀት ግን ጽንፍ በደረሰ አቋም የሀገሪቱ ታሪክ ጉድለቶች ላይ ብቻ በማተኮር የሀገር መፈራረስ እንደመፍትሄ ሊታይ ይገባዋል የሚል አቋምን ሲገፋ ቆይቷል።በዚህም አንጻር በሀገሪቱ ውስጥ የሚታየውን የተዛባ ግንኙነትና የመብት መጣሰ ለመስበር የሚቻለው በብሄር ተደራጅቶ በመታገል የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት

መቀዳጀት ሲቻል ነዉ ብሎ የተቀበለ ድርጅት ነዉ ።ይህ ሙብት ደግሞ እስከመገንጠልና የራስን ነጻሀገርና መንግስት እስከመመስረት ሊሄድ ይገባዋል የሚል አመለካከት አለዉ።

በኮሎኔል መንግስቱ የሚመራው ወታደራዊዉ መንግሥት (በኋላም ኢሰፓ) ሥልጣን ላይ በቆየበት ዓመታት ብሔረተኛ ንቅናቄዎች አይለዉ የተነሱበትና እያደርም ጥንካሬ እያገኙ የመጡበት ወቅት እንደነበር አይዘነጋም;: በየአቅጣጫዉ በገጠመዉ ዉጥረትም ዉሎ አድሮ በ1991 ደርግ ከሥልጣን ሲወገድ ወደ ቤተመንግሥት የዘለቀዉ እንቅስቃሴ ዋነኛው ሀይል ብሔረተኛው ድርጅት የትግራይ ነፃ አዉጪ ግንባር/ ሕወሃት ሆነ ::

ከላይ እንደተመለከትነዉ **ሕወሃት** ከጅምሩ ፖለቲካዊ ፍልስፍናዉ በብሔር ዙሪያ የተቃኘ በመሆኑ በኢትዮጵያ “ዋነኛ ችግር” የሚለውን የብሔሮችን ሙብት ያለመከበር ሁኔታ ለመፍታት ብቸኛ አማራጭ በብሔር ዙሪያ መደራጀት እንደሆነም አሳወቀ:: ይህንኑ ዓላማዉን ለማሳካት የሚያስችለዉም ዕድል (የመንግስት ስልጣን) በአውሮፓ አቆጣጠር በ1991 ሲያገኝ በአምሳሉ የሚንቀሳቀሱ የብሄር/ብሄረሰብ ድርጅቶች በአፋጣኝ ፈልፍሎ በዋናነት ብሄር ተኮር የሆነ በመጀመሪያ አስራ አራት በሓላም ዘጠኝ ክልሎችን ሸነሸነ ። ይህ ያስተዳደር ስርአት ሕጋዊነት እንዲያገኝም ሕገ-መንግሥታዊ ማሰሪያ ሰጠዉ:: ያለ በቂ ጥናትና ሕዝባዊ ተሳትፎ ብሔር-ተኮር ፌድራሊዝምን እንደ መንግሥታዊ ሥርዐት አወጀ::

ፌደራላዊ አደረጃጀት በተለያዩ ሃገሮች የተለመደ መንግሥታዊ አሠራር ቢሆንም ይህ “….አዲሱ በብሄር ልዩነቶች ላይ የተመሰረተው የፌዴራል ስርዓት ግን የቆየውን የሕዝብ ትሥስር የሚገባውን ቦታ ሳይሰጥ አንዳንድ ቦታ በተለያዩ ማህበረሰቦች መሀል የነበረውን ህብረትና ትስስርን አዳክሞና ልዩነቶችን አጠናክሮ፤ ለአንድ በብሄር ለተዋቀረ ድርጅት የበላይነት ያጎናጸፈ መሳሪያ ሆኖታል …”[2] ከዚያም አልፎ ዛሬ በኢትዮጵያ ለተከሰተዉ አለመረጋጋትና ፖሊቲካዊ ቀዉስ ዓይነተኛ ምክንያት ሆኗል::

የክልሎቹ አመሠራረት በዋናነት የራስን ፖሊቲካዊ ፍላጎት ከማከናወን ያለፈ ትኩረት ስላልነበረዉ ቀጥሎ የተዘረዘሩት መሠረታዊ ችግሮች እንዳሉት ያጤኗል::

- ቋንቋን በዋናነት እንደ ብቸኛ መመዘኛ የወሰደ መሆኑ
- የሕዝብን የቆየ ማኅበረሰባዊና ሥነልቦናዊ ትስስር ያላገናዘበ መሆኑ
- የቆየ አሰፋፈርና ኢኮኖሚያዊ መስተጋበርን ያላጤነ
- ባበጃቸዉ ክልሎች ዉስጥ የተካተቱ ሌሎች አነስተኛ የሚባሉ ቋንቋዎችን ግምት ዉስጥ ያላስገባ መሆኑን
- የብሔርሰብ ማንነትን እንጂ ብሔራዊ ማንነት የማያጎለብት መሆኑ እንገነዘባለን

ኢትዮጵያን ለማፈራረስና ሕዝቧን ለእርስ በርስ እልቂት የአመቻቸው የህወሓት/ኢህአዴግ አምባገነናዊ ስርአት የፈጠረውን መሰረታዊ ችግር አሁንምገዢው ፓርቲ አግባብ ባለው ሁኔታ አላየውም፤ ቢያየውም ችግሩን ንቆ ትቶታል።[3] እንዲያዉም ለችግሩ መፍቻ ከድርድርና ፖለቲካዊ መፍትሄ ይልቅ እየተጠቀመ ያለዉ ኃይልንና አጥፊውን ፖሊሲ በተጠናከረ መልክ ማስቀጠል ነዉ:: ይህም አሁን ያለው ችግር እጅግ የተወሳሰበ የማያባራ ግጭትና አደጋ በሀገሪቱና በህዝቡ ላይ እውን እንዲሆን አድርጓል።

*ዓለም ሃብቱ Ethnic Federalism in Ethiopia: Background, Present Conditions and Future Prospects*
1፣2፣3 ዶ/ር አክሎግ መጣጥፍ የተወሰደ

**የኢህአዴግ /ህወሀት የብሄር ተኮር ፌደራሊዝምና ያስተዳደር ክልሎች አሸናሸን ያስስከተለው ችግር ምንድነው?**

የህወሀት/ኢህአዴግ መንግስት ተግባራዊ ያደርገው ብሄረሰብ ተኮር የክልሎች አሸናሸን ያስከተላቸው እጅግ ብዙ ችግሮች ቢኖሩም በዋናነት ከሚነሱት ውስጥ የሚከተሉት ይገኛሉ፡

1. የተፈጠሩት ክልሎች መሰረት የተደረገው "ብሄር ብሄረሰቦች" በመሆኑና ክልሎቹም ያካባቢ ተወላጅና "መጤ" የሚል እንደምታን ስለሚገፋፉ ፣ በተለያዩ የክልሉ ነዋሪ ኢትዮጵያውያን መሀል ህይወት እስከማጥፋት የደረሰ ሰፊ እልቂት እና መፈናቀልን አስከትሏል። ለዚህ ደግሞ እጅግ ሰቅጣጭ ተግባር የተፈጸመባቸውን ቦታወች አርባጉጉን፣ ገለምሶን፣ ወተርን፣ መቻራን፣ ጎሎልቻን፣ ቤንች ማጂን፣ ጉራፈርዳን፣ አመያን ማየት ይቻላል። Ethnic-Based Federalism in Ethiopia and its Impact on National Integrationበሚል ርእስ የቀረበ ጥናት የተከሰተውን ግጭት አንደሚከተለው ያቀርበዋል፡

" በኢትዮጵያ ውስጥ አንዱ ከሌላው ብሄር ተስማምቶ በፍጹም መኖር የማይችል ነው የሚመስለው። በዳርም ይሁን በመሀል አገር የሚገኙ ክልሎች እርስ በርስም ይሁን ከሌላ ብሄር ተወላጆች ጋር በዛ ያሉ ግጭቶች ውስጥ ስለገቡ መረጋጋት አይታይባቸውም። ግጭቶቹ በዋናነት ፡የሚቀሰቀሱት ማንንትን መሰረት ካደረገው የፌዴራል አወቃቀር ጋር ተያይዘው ነው። ለምሳሌ የሶማሌ ፣ ጋምቤላ ቤነሻንጉል ጉሙዝ፣ኦሮምያ አማራ፣ ደቡብ ህዝቦች አፋር እና ሀረሪ ክልሎች በእርስ በርስና አንዱ ካንዱ ጋር በሚደረግ ግጭት ተከስቶባቸዋል፡ በዚህም ተጎድተዋል። በነዚህ ክልሎች የክልሎቹ አወቃቀር በብሄር ላይ ለተመሰረተ ግጭት አጋልጧቸዋል።ለምሳሌ በኦሮሞና አማራ መሀል በ1992 እና በ1993 ፣ በአፋርና ኢሳ መካከል በ2002፣ በኑዌርና አኙዋክ መሀል በ2002፣ በከረዩ ኦሮሞና በአፋር መሀል በ2002፣ በአኝዋክ እና ደገኛ ተብለው በሚጠሩት መሀል በ2002፣ በኦሮሞና ሶማሌ ፣ማህበረሰቦች መሀል በ2005፣ በያንጋታሞና በካራ መሀል በ2007፣ በመጀንገር እኛ ደገኛ ተብለው በሚጠሩ መሀል በ2013፣ ግጭት እንደተካሄደ በዚህ ጉዳይ ላይ በሚከተሉት ጸሀፊወች የቀረቡት ጥናቶች አሳይተዋል Abbink (1997, 2006), Dereje (2005),Vaughan (2006), Clapham (2004, 2006)".http://www.academia.edu/22469398/Ethnic-Based_Federalism_in_Ethiopia_and_its_Impact_on_National_Integration

2. የተፈጠሩት ክልሎች መሰረት የተደረገው "ብሄር ብሄረሰቦች" የራሳቸውን አስተዳደር የመወሰን መብት አላቸው የሚል (አንቀጽ 47) አመለካከት መሰረት አድርጎ በመሆኑና በየቦታው የሚገኙ ክልሎች በውስጣቸው የሚገኙ "ብሄር ብሄረሰቦችም" የራሳቸውን አስተዳደር ለመመስረት በሚያደርጉት ሙከራ ሰለሚያነሳሳ በሀገሪቱ ውስጥ ለማያቋርጥ ቅራኔ ፍጥጫና ግጭት መሰረት ሆኗል። ይህ ደግሞ በስልጤ፣ በተለያዩ የኦሮሚያ አካባቢወች፣ በደቡብ ክልል በኮምሶ፣ በሶማሌና ኦሮሞ ክልሎች መሀል ወዘተ የብዙ ዜጎችን ህይወት ያጠፋ ግጭትን ቀስቅሷል። ይህ ሁኔታ አሁንም በስፋት በመቀጠል ላይ ነው።

ከላይ የተጠቀሰው ጥናት ይህን ግጭት መሰረት አንደሚከተለው ያቀርበዋል " በሀገሪቱ ውስጥ አሁን ባለው ሁኔታ የሚታየው የብሄር ግጭት ምክንያት መሰረት ብሄር/ብሄረሰቦች ስልጣንና ሀብትን በተመለከተ በብሄር ብሄረሰቦች መካከል የሚታየው እጅግ ከፍተኛ ውድድር ነው። በዚህ አኳያ ማንንትን መሰረት ያደረገና ተወዳጅነትም የሌለው ፌዴራሊዝም፣ ብዙሀዊነትን ባግባቡ ማስተናገድን ስልጣንን መጋራትን ለማስተናገድ ያላስቻለውንና ባንጻሩ ደግሞ ግጭትን የሚያስፋፋውን ፖሊሲ ቀርጾ ተግባራዊ ያደርገው ድርጅት ፣ ህወሀት/ኢህአዴግ ነው የህን ሁሉ ያመጣው። ሁሉም የተለያዩ ብሄረሰብ ተወላጆችን የያዙ ክልሎች ድንበርን ውክልናን እና የተፈጥሮ ሀብት ክፍፍልን መሰረት ያደረገ ግጭት ውስጥ ናቸው። ባንድንድ ቦታወች ደግሞ የሀገሪቱ ህገመንግስት አንቀጽ 47 በሚፈቅደው መሰረት ከሚገኙበት ክልል ተገንጥለው የራሳቸውን ክልል ለመለስረት ጥረት ያደርጋሉ።

3. የተፈጠሩት ክልሎች የህዝብን ታሪክና ፍላጎት፣ ለስተዳደር የሚኖረውን ጠቀሜታ ባማከለ መልክ ሳይሆን በስልጣን ላይ ያለውን ህወሀት ኢአህአዴግናና ሸሪኮቹ በመሰላቸው መልክ ለራሳቸው ፖለቲካዊ ጥቅም እንደፈለጉ የሸነሸኑት ስለሆነ ከማንንት ጋር የተያያዘ፣ በወቅቱ ድምጻቸውን ለማሰማት ያልቻሉ ክፍሎችን ጥያቄ መሰረት ያደረገና ሌሎችንም ሰፊ ጉዳዮች ያጠቃለለ ቀጣይ ግጭትን አስከትኋል። ይህ ጉዳይ በወልቃይት ጠገዴ፣ በኮንሶ፣ ወዘተ በሰፊው ተከሰቷል።
   ክራይስስ ግሩፕ የተሰኘው ድርጅት በአውሮፓውያን አቆጣተር በ2009 ባወጣው ጥናት እንደደመደመው " ኢህአዴግ ተግባራዊ ያደረገውብሄር ተኮር ፌደራሊዝም በሀገሪቱ ውስጥ ይታዩ የነበረሩትን ግጭቶች በመሬትና ፣ የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት፣ በድንበር ጉዳይ፣ በመንግስት በጀትና መሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ግጭቶች መቀነስ ሳይሆን ይበልጥ አሰፋፍቶቷቸዋል"

https://www.crisisgroup.org/africa/horn-africa/ethiopia/ethiopia-ethnic-federalism-and-its-discontents Nairobi/Brussels, 4 September 2009"

4. የተፈጠሩት ክልሎች መሰረት "ብሄር ብሄረሰቦች" የሚለው ነጠላ መመዘኛ በመሆኑ ባንዳንድ ክልል (ለምሳሌ ባኦሮሚያ በቤኒሻንጉል፣ በሀረሪ) ከሌሎች ብሄረሰቦች የተወለዱ ወይም ከተደበላለቀ ቤተሰብ በመወለዳቸው ወደአንድ "ብሄር" ራሳቸውን የማይመድቡ ኢትዮጵያውያን በክልሉ ፓርላማ ውክልና እንዳይኖራቸው ያደርጋል። ለምሳሌ በቤኒሻንጎል የሚገኙ የሌላ ብሄር አባሎች በቁጥር ከቤኑሻንጉላ ብሄር አባላት ቢበልጡም በፓርላማው ውስጥ ግን ውክልና የላቸውም፣ በሀረሪ ክልል ደግሞ 20 % የሚሆኑት አማሮች ሲሆኑ በክልሉ ፓርላማው ውክልና የላቸውም። አፍ መፍቻ ቋንቋቸውም በክልላዊ መንግስቱ እውቅና ተሰጥቶት ይፋዊ የህዝብ መገልገያ ቋንቋ አልተደረገም። በመሆኑም ቋንቋወቹ በትምርት ቤቶች አይሰጡም። ባኦሮሚያና በሶማሌ ክልሎችም ተመሳሳይ ሁኔታ ነው ተግባራዊ የተደረገው። ይህ ደግሞ ከ150 አመት በፊት ፡"ተደረገ" የሚባለውን በግድ የራስን ማንነት የማስቀየር ተግባር ዛሬ በህግ ተደግፎ እየተተገበረ እንደሆነ ያሳያል።ለዝርዝር መረጃ የየክልሉን ህገመንግስት ይመልከቱ ። ይህ ከፍተኛ ወንጀል የግጭት መንስኤ ሆኖ እንደሚቀጥል ለማንም ግልጽ ነው።

https://chilot.me/2012/02/09/revised-constitutions-of-regional-states/
https://chilot.files.wordpress.com/2012/02/oromia-national-regional-state-constitution.pdf
https://chilot.me/2012/02/09/revised-constitutions-of-regional-states/harari-regional-state-constitution/

5. በተፈጠሩት ክልሎች ወደውስጥ መመለልከትንና ብሄረታኝነትን የሚያጎላ ሲሆን ባንጻሩ ግን የሀገሪቱን የተለያዩ አካባቢወችና ቋንቃ ተናጋሪወች የጋራ እሴቶች ማዳበርን ደግሞ የማያበረታታ በመሆኑ አንድ ሐገር እንደ ሐገር ለመኖር የሚያስፈልጋትን የዜጎች የጋራ መተሳሰርና በጋራ ሊያደንቁትም ሆነ ሊያከብሩተ የሚገባ እሴትን ከመገንባት ይልቅ በመቦርቦር ላይ ያተኮረ ነው። በመሆኑም ለህዝብ መተሳሰርና የሀገሪቱ አንድነት ላይ ታላቅ አደጋን ጋርጦ ይገኛል። ሕብረተሰቡ በቋንቋ መሰረት እጅግ እየተከፋፈለ እንደሚገኝና ከዚያም አልፎ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሳይቀር እንደተስፋፋ በ2014 nternational Journal of Innovative reasearh and development የተሰኘ የጥናት ሀትመት ላይ የሰፈረ Ethiopian Ethnic Federalism and its Implications for University Students: The Case of University of Gondar የሚል ጥናት እንደሚከተለው ይገልጠዋል " The Case of University of Gondar ፣ Bitwoded Admasu Dagnaw University of Gondar, College of Social Sciences and Humanities, Department of Civics and Ethical Studies, Ethiopia፡www.ijird.com November, 2014 Vol 3 Issue 11) "የጥናቱ ግኝት የሚያሳየው የብሄር ፖለቲካ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ከ1991 ወዲህ ተማሪወች የእለት ተእለት ግንኙነታቸው

በተመለከተ በክፍል ውስጥ በምግብ ቤት በመኝታ ክፍሎቻቸው፣ በቤተ መጻሀፍት አካበቢ አሉታዊ ተጽእኖ እንዳለው ነው። ያንዱ ብሄር ተወላጅ ተማሪወች ለሌላ ብሄር ተወላጆች ግዴለሽነትን አዳብረዋል ። ተማሪወች የሚያግባባቸው ቋንቋ ለመናገር ባለመቻላቸው የተነሳ  የባህል ልውውጥ ማካሄድም አስቸጋሪ ሆኗል'።

6. በሀገሪቱ ውስጥ የተመሰረቱት ክልሎች የብሄር ብሄረሰብን ቁንጽል ገጽታ እንደ ዋና መመዘኛ አድርጎና ሌሎችን ጠቃሚ ጉዳዮች (የህዝብ ብዛት፣ የኢኮኖሚ ተመጣጣኝነትን፣ እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ወዘተ) በግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ነው። ይህም በመሆኑ ፣ዘጠኙ ክልሎች በስፋት ፣ በሰው ሀይልና ወዘተ ተመጣጣኝነት የላቸውም። የሀገሪቱ የፖለቲካ አወቃቀርም የህዝብን ቁጥር መሰረት አድርጎ የተዋቀረ ባለመሆኑ  አሁን ባለው ሁኔታ በሀገሪቱ ውስጥ በቁጥርና በቆዳ ስፋት የተነሳ የበላይነት የሚይዙ ክልሎችና (ብሄር ብሄረሰቦች) በቆዳሰፋትና በህዝብ ቁጥር ማነስ የተነሳ ደግሞ ሁልጊዜ የበታች ሆነው የሚቀጥሉ ብሄር ብሄረሰቦች እንዲኖሩ አድርጓል። ከዚህም አልፎ አሁንም ሆነ ረዘም ባለው ጊዜ ሀብታምና ድሀ፣ ክልሎች እጅግ የለሙና ወደሓላ የቀሩ ክልሎች የሚፈጠሩበትን ሁኔታ መሰረት ጥሏል። ይህ ደግሞ ሀገሪቱ እኩልነት የሰፈነባት አልነበረችም የሚለውን አስተሳሰብ ባዷስ መልክ የሚያስፋፋው እንጂ የሚቀንሰው አይሆንም።ባጠቃላይም አሁን ያለው የክልሎች አሸናሸን በሀገራችን ውስጥ ኢኮኖሚያዊም ይሁን ፖለቲካዊ ፍትሀዊነትን እንዳይኖር ያደርጋል።

7. ከላይ እንደተገለጸው ክልሎች በውስጣቸውም ሆነ  በእርስ በርስ ግጭትና፣ አለመረጋጋት ሲናጡ በሀገር ደረጃ የፖለቲካ ስልጣኑን የሚቀጣጠረው ክፍል (ህወሀት/ኢህአዴግ)  ዜጎችን ከፋፍሎ በመግዛት እርስ በርስ ተፋጠው እንዲኖሩና እርሱ ግን በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው መስክ ሲያሰፈልግ ገላጋይ ሌላ ጊዜ ደግሞ  አዛዥ ሆኖ የበላይነቱን ይዞ እንዲቀጥል እድል ሰጥቶታል። ስርአቱ በፌዴራሊዝም ስም የተዋቀረ ይሁን እንጂ ሙሉ በሙሉ በህአዴግ/ህወሀት ቁጥጥር ስር የወደቀ ነው። የክልል ፓርቲዎች (ኦህዴድ፣ በአዴን፣ ደቡብ ህዝቦች ወዘተ) የ"መሪ ፓርቲው" የህወሀት/ኢህአዴግ ተቀጽላወች ስለሆኑ ምንጊዜም የሀገሪቱን ፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ ማህበራዊና ዲፕሎማሲያዊ አቅጣጫ 'መሪው ፓርቲ" እንዲቀጣጠር አድርጎታል። http://www.on-federalism.eu/attachments/181_download.pdf

8. የመሬት ባለቤትነትና የክልሎች አሸነሸን ።

በአሁኑ ሰአት በሀገሪቱ ውስጥ ለምን እጅግ ሰፊ የሆነ የድንበር ግጭት ተከሰተ የሚለውን ለመረዳት ደግሞ በዚህ ስርአት መሬት የብሄር/ የብሄረሰብ ነው መባሉ ይህም "እኛና እነሱ" የሚለውን ድንበር ይበልጥ እንዲሰፋ እንዳደረገውና የማያባራ ግጭትን ለመቀስቀስ ዋነኛው ምክንያት ሆኗል።

ሕወሀት/ኢህአዴግ ተግባራዊ ያደረገው የብሄር ተኮር ያስተዳደር ክልል አሸናሸንና "መሬትም የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሳይሆን   የዚሁ ክልል ብሄር  ንብረት ነው የሚለው ፖሊሲ እጅግ ብዙ ዜጎች ለዘመናት የኛም ንብረት ነው ብለው እንደልብ በመዘዋወር    የሚገለገሉበትን መሬት  አሁን  የሌላ ክልል ነው ተብለው   የመጠቀም መብታቸውም ተገፍፏል ወይም እጅግ ተገድቧል። የህዝብ ተፈጥሯዊ የሆነ መዘዋወር (movement)  በ"ብሄር" እየታጠረ መስመር ተሰምሮበት ማገር ሲቀርጥበት፣ አደን ሲያድንበት ባደገበት ምድር አሁን እንግዳነት እንዲሰማው፣ የወል የባለቤትነትን ሲሜት እንዲያጣ ሲሆን   በመቶና በሺህ ኪሎሜትር ርቀት ያለ ሰው ደግሞ አሁን መሬቱ " የተሰጠው ብሄር" ተወላጅ በመሆኑ ብቻ ሙሉ ባለቤትነት ተሰጥቷቸዋል ።

የአስተዳደር አሸናሸኑ ትርጉም የአስተዳደር ድንበር መሆኑ ቀርቷ መሬት ወይም ድንበር የዚህ ብሄር የጋራ ንብረት የሚያደርግ ሲሆን በአካባቢው ወይንም ከክልሉ ውስጥ ካለው ህዝብ ጥያቄነት አልፎ በአመት ለተወሰነ ወራት ወዳካባቢው በመሄድ ይጠቀም የነበረውን ህዝብም ሆነ መኖሪያውን ሌላ ቦታ አድርጎ ጥሬር ዘለል በመሆን የሚያርሰውን ወይንም በተለያየ መልክ ያካባቢውን መሬት ይጠቀም የነበረውን ሁሉ ባለቤትነትን የሚነጥቅ ነው። ይህም "የኛን መሬት ነጥቀው ለእነ እገሌ ሰጡት " ወደሚያሰብል አመለካከት የሚገፋፋ፣ አንዱን ብሄር በሌላው ኪሳራ ተጠቃሚ አድርጎ የሚያስልፍ በመሆኑ እጅግ ስሜትን የሚነካና ጥልቀት ያለው ብሶትና ቅራኔ እንዲሰፋፋ አድርጓል። ዛሬ በስሜኑ የሀገራችን ምድር በወልቃይት ጠገዴ፣ በሶማሌና ኦሮሚያ ተብለው በተሸነሸኑት ክልሎች ድንበር ወዘተየሚታየው እጅግ የተካረረና የብዙ ሰወችን ህይወት ወደ ቀሰፈ ግጭት እንዲያመራ አድርጎታል።

9. **የክልል አሸንሽንና የህዝብ ሰፈራ፡**

ዜጎች በሁሉም ኢትዮጵያ ውስጥ የመኖር መብታቸውን ገድቦ የሰፈራ ፕሮጋራሙ በየክልሉ ውስጥ እንዲታቀብ በሚል ሂሳብ በተለይም በወልቃይት ጠገዴ ቋራ ወዘተ ካንድ ብሄር የሚወለዱ ግለሰቦችን በሰፊው እዲሰፍሩ ስላደረገ ከፍተኛ የህዝብ ተቃውሞን አስከትሏል። ለምሳሌም በአውሮፓ አቆጣጠር 2003 እስከ 2005 ባለው ጊዜ ውስጥ ከሌሎች የትግራይ ክፍሎች ወደ ወልቃይትና ጠገዴ የሰፈረው ህዝብ ቁጥር 40 ሽህ ቤተሰቦችን 200ሽህ ግለሰቦችን የያዘ ነው።
https://www.researchgate.net/publication/263813078_Resettlement_of_Peasants_in_Ethiopia

ይህ ደግሞ ስርአቱ ሁሉንም ነገር በብሄር ብቻ እንዲታይ ባደረገበት ፖሊሲው ምህዳር ሲታይ ያካባቢውን የጎሳ ስብጥር ለመቀየር ሆን ተብሎ የተደረገ ነው ወደሚለው መደምደሚያብዙዎችን እንዲሄዱ አድርጓል። ሰወች ሰፈራንና እርስ በርስ መተዛዘንን በጎሳ አኳያ እየመዘኑ እንዲያዩ የሚያደርገው የስርአቱ ብሄር አዘል የክልል አሸናሸን ድብልቅ ቋንቋ ተናጋሪ በሚገኝበት እንደ ወልቃይት ባለው አካባቢ ደግሞ የሁሉም ኢትዮጵአዊ ባካባቢው ሰፍሮ የመኖር መብቱ ተገድቦ ለአዲሱ ክልል ተወላጆች ግን እድሉን ሲሰጥ ያስከተለው አሉታዊ እንደምታና የቅሬታ መንፈስን ነው።

ይህ ከላይ የተጫኘና አካባቢውን ምድር ያዲሱ ክልል ንብረት በማድረግ ባካባቢው ለዘመናት የኖረውን ተፈጥሯዊ የህዝብ መዘዋወርና ሰፈራ (natural migration and settlement) አድርጎ ከላይ ወደታች በመንግስት በተጣለ ገደብ ስር በመካሄዱ አለሰፈላጊ ቅሬታና ምስቅልቅል ትልቅ ብሶት፣ ትልቅ ተቃውሞን አስነስቷል።

ከላይ የተጠቀሰውን ይበልጥ የከፋ የሚያደርገው ደግሞ ምንም እንኳ ህወሀት/ኢህአዴግ ሰፈራ ሲካሄድ ካካባቢው ህዝብ ጋር በመመካከር ነው ይበል እንጂ ወልቃይትና ጠገዴን በተመለከተ ግን የህወሀት ባለስልጣኖች ሰው ከማስፈራቸው በፊት ላካባቢው ነዋሪ ለወልቃይቴው መሬት አልባ መሬት እንዲከፋፈል ያካባቢው ህዝብ የጠየቀውን ጥያቄ ወደጎን ገፍትረው ነው የፈለጉትን ያደረጉት። Allula Pankreset,Assefa Tolera, Gebre Yntiso Kassahun Berhanu http://www.fssethiopia.org/publicationfile/n4%20eng.(1).pdf ይህም በመሆኑ ባካባቢው ነዋሪወች በተለይም ባማርኛ ቋንቋ ተናጋሪወችና በፖለቲካ ተቃዋሚወች በኩል ስርአቱ የሚያካሂደው

ያካባቢውን የቋንቋ ስብጥር ለመለወጥ የሚደረግ እርምጃ ነው ወደሚል መደምደሚያ እንዲያዘነብሉ አድርጓል።

**የወልቃይት ጠገዴ ጉዳይ፥**

ታሪክን መሰረት ያደረገ ጥናታዊ ትንታኔ ባብላጫው ተቀባይነት ያለው አቀራረብ ከመሆኑም ባሻገር በቅርብ ጊዜ ለተካሄዱና በመካሄድም ላይ ላሉ አዋካቢ ሂደቶች ከምስክርነት አልፎ ከእውነት ጋር የሚያቀራርብ ለመሆኑ አማራጭ የሌለው ነው ብንል አንሳሳትም።

ወልቃይት ጠገዴ የአማርኛም የትግርኛም ተናጋሪ ኢትዮጵያዊያን በመፈቃቀር አብረው የኖሩበት አካባቢ ስለመሆኑና ይህም አካባቢ በታሪኩ በጎንደር፣ ቀደምሲልም በጌምድርና ሰሜን አስተዳደር ስር ከዚያ በፊት ደግሞ ባካባቢው ባህላዊ አስተዳደሮች ስር ሲተዳደር እንደቆየ ሰፊ ታሪካዊ ማስረጃወች ይመሰክራሉ። ከነዚህም ታሪካዊ መረጃወች ውስጥ የሚከተሉትን መመለከት ይቻላል።

በ14ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ በንጉስነት የአዋሽ አካባቢ ተወላጅ የሆኑትን ንጉስ ዘርአ ያእቆብንና ዘመናቸውን እንቃኛለን። እነህ ንጉስ በዘመኑ በርካታና አበይት ስራወችን አበርክተው ያለፉ ሲሆን የታወቁ ፈላስፋና የኪነ ጥበብ አፍቃሪ እንዲሁም የብዙ መጻህፍት ደራሲም ናቸው።

በወቅቱ በእርሳቸው ዘመን ከተጻፉት መጻህፍት አንዱን ብንጠቅስ፣ በተለይም በአክሱም ንብረ እድ የተጻፈውን "ዜና አክሱምን" ያስተውሷል። የዜና አክሱም አብዛኛው ይዘት ሀይማኖታዊ ሀተታን ያዘለ ቢሆንም የዘመኑን የኢትዮጵያን ማለትም የ14ኛው ክፍለ ዘምን ኢትዮጵያ ምን ትመስለል እንደነበረ አጠቃላይ ወሰንና ክፍላተ ሀገራትን በተለይም ድንበሮችን በጥንቃቄ እንደሚከተለው ዘግቧል።ይህም የወቅቷን ትግራይን ከባቢ ካርታን ጨምሮ እንደሚከተለው አቅርቧል። "አከሱምን ማእከል ያደረገውና ወጣ ብሎም በሁለተኛና ሶስተኛ ዙር ከባቢ ግዛቶች በየትኛውም አቅርቦት ወልቃይት ጠገዴን አይጠቀልልም። ማለትም የትግራይ አካል አድርጎ አያቀርባቸውም ። በተመሳሳይ ሁኔታም በ15ኛው ክፍለ ዘመን የታተመው the world through maps of history of cartography የተሰኘውና በ John R Short የተጻፈው የአለም ጂኦግራፊ ይህንኑ የአክሱም ንብራእድን ጽሁፍ በመመርኮዝ የትግራይ ክፍለ ግዛቶችን በወቅቱ ያረጋግጣል። ይህም ማለት በ14ኛውም ክፍለ ዘመን ሆነ በ15ኛው ትግራይ የግዛት ለውጥ እንዳልነበራት ይጠቁማል።

ወደ 16ኘው ክፍለ ዘመን ስንመጣም በተመሳሳይ የወቅቱ የኢትዮጵያ ንጉስ እጅግ ታላቅ በጣም የሚታወቀውና የሚደነቀው ይዞታው የትግራይ መቀመጫው መሆኑን ጠቅሶ ከሀማሴን እስከ እንደርታ (3.2 ማይልስ) በስተምስራቅ የደናክል በረሀ ወደ ውቅያኖስ መድረሻ ማለትም ቀይ ባህር መድረሻ ደቡባዊ ጫፍ በስተ ምእራብ በተከዜ ወንዝ ይካለለልል ።እንዲያውም ትግራይ በቅርጽና አቀማማጥ ወደ ክብነት ታደላለች ይልል። ይህም "የ17ኛው ክፍለ ዘመን በታሪካዊ ጂኦግራፊ ይዘት" በሚለው መጽሀፍ በ 1634 EC የቀረበ ነው።

አሁንም ትግራይን ከወልቃይት ጠገዴና ጸለምት በየትኛውም መልኩ የቀረበ ግንኙነት ወይንም የአስተዳደር ሁኔታን አያመለክትም።

ቀረብ እያልንም ስንመጣ ወደ ዘመነ መሳፍንት እንደርሳለን፡፡በዚህም ወቅት አጼ ቴወድሮስ እስከነገሱ ድረስ ማለትም ማእከላዊ አስተዳደር በማይታሰብበት የመሳፍንቱን ዘመን ማ፣ ማንን ይገዛ እንደነበረ ሲጽፍ ስለ ትግራይ ባቀረበው ትንታኔ "ትግራይ በባህረነጋሽ ማለትም በምስራቅ በመረብ ወንዝ በምእራብ በተከዜ ትዋሰናለች ይላል፡፡ ስፋቷም ከምስራቅ እስከ ምእራብ 120 ማይል ሲሆን ከሰሜን ወደ ደቡብ ደግሞ 200 ማይል ነው ይላል፡፡

በመጽሀፉ ምእራፍ 10 ላይ ጀምስ ብሩስ የኢትዮጵያ ግዛታዊ ክፍፍል በጠቅላይ ግዛቶች በሚል ርእስ ሲያስቀምጥ "የመጀመሪያው ክፍል ትግራይ ሲሆን ይህም በቀይ ባህርና በተከዜ ወንዝ ሲሆን በስተምእራብ በአባይ ወንዝ ከኦሮሞ አዋሳኝ አማራ ይባላል ይልና፤ ወረድ ብሎ ተከዜ የተፈጥሮ ድንበር የሆነ የትግራይና የአማራ አዋሳኝ ነው ይላል፡፡

ከዚያም በአጼ ቴወድሮስ ዘመን (1881-1868) በእንግሊዟ ንግስት በንግስት ቪክቶሪያ ትእዛዝ በእንግሊዝ ሀውስ ኦፍ ኮመንስ ሎወር ኮርት መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ ኤ ሲ ኩክ የተባለ ኮሎኔል የተጻፈና የተቀነባበረ መጽሀፍ topographical and Statistical Department of the war office የጸጥታ ክፍል ተጠርዞ የቀረበው ይህ ጽሁፍ በተለያዩ የወቅቱ የኢትዮጵያ ዝርዝር በአጼ ቴወድሮስም ሆነ ከእርሳቸው ቀደም ሲል በማን ስር ይተዳደሩ እንደነበረ ያትታል፡፡ ለምሳሌም የሚከተለውን ይመለከቷል፡
"የአማራ ክፍለ፤ ሀገር ሰሜን ዋልድባ፣ ጭልጋ ቋራ ፎገራ ዳሞት ጎጃም በጌምድር በሸሎ .......ዋልድባ የሚገኙት ከሰሜን በሰሜን ምእራብ በኩል በተከዜና በአንገረብ መሀል ሲሆን እስከሁለቱ ወንዞች መገናኛ ይዘልቃል፡፡ ወልቃይት ደግሞ ከዋልድባ በስተምእራብ ሲሆን ከጫፍ እስከጫፍ ደግሞ በተኩራ እና ጓንግ ወንዞች የተከለለ ከዋልድባ በላይ ጫካ የበዛበት ነው"፡፡
Routes in Abyssinia (printed in 1867 GC ) page 188 http://archive.org/stream/routes in absyssinia cookrich page 186/mode/zup/search/1 የሚለውን ሊንክ በመጫን ሙሉ መፕሀፉን ማውረድ ይቻላል፡፡

ይኸው መጽሀፍ በወቅቱ የነበረውን የትግራይ ክፍለ ሀገር ድንበርና ግዛት በግልጽ እንደሚከተለው ያሰቀምጠዋል፡" ዋና ከተማዋ አድዋ የሆነው ትግራይ ወሰኖች በምእራብ ሽሬ በደቡብ ምእራብ ተምቤን እና አዴት(Adet )፣ በደቡብ በኩል ግራልታ (Geralta) በደቡብ ምስራቅ በሀራማት (Haramat) በምስራቅ አጋሜ፣ በሰሜን በመረብ ወንዝና በበለሳ ይዋሰናል"፡፡ ይህ ደግሞ በገጽ 187- 188 ተገልጿል፡፡

በተጨማሪም በ1880 ወቹ ከተጻፉ መጻሀፍት አንዱ "the earth and its enhabitants" የሚል ሲሆን ከያዛቸው ዘጠኝ ክፍሎች ክፍል አራት ላይ የሰሜንና የምስራቅ አፍሪካ የወቅቱን ጂኦግራፊ ይተነትናል፡፡ በአጼ ዮሀንስ ዘመን የነበረውንም የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት ሲዘረዝር የሚከተለውን አስፈሯል፡፡ " የአማራ መንግስት ጠቅላይ ግዛቶች የሚከተሉት ናቸው፡ ደምቢያ፣ ጭልጋ. ዳጎሳ፣ ቋራ ወገራ፣ ዋልድባ እና ወልቃይት"

የህም ማለት በአጼ ዮሀንስ ዘመንም ወልቃይት ጠለምት ዋልድባ ወዘተ በትግራይ ስር እንዳልነበሩ ያመለክታል፡፡ በአስተዳደርም በጎንደር ስር እንጂ በትግራይ ስር እንዳልነበሩ ጸሀፊው ከላይ የተጠቀሱትን ብቻ ሳይሆን በጊዜው ለህትመት ላበቃቸው የአለም ጆኦግራፊን አስመልክቶ በለንደንና በፓሪስ የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ እድርጎታል፡፡ ይህ የጂኦግራፊ ሰው ፕሮፌሰር ኤሊስ ሬክለስ ይባላል፡፡

ከላይ በታሪክ መረጃ ተደግፎ የቀረበው የወልቃይት ጠገዴ ቀደምት አስተዳደርና ትስስር ምን እንደሆነ ያሳየናል። ይህን ታሪካዊ ትስስር ወደጎን ትቶ ተግባራዊ የተደረገው የህወሀት የክልል አስተዳደር አሸናሸን ነዋሪውን ህዝብ መሰረታዊ የሆኑ የማህበራዊ ፍትህ ጥያቄወችን (የመፈናቀል፣ የመሬት ነጠቃ፣ የማናንት ጉዳይ ወዘተ) እንስቶ ህይወት እስከመገበር በደረሰ ሁኔታ እንዲታገል አድርጎታል።

የህወሀት/የኢህአዴግ አንዱ የክልል አሸናሸን ድክመት፣ቀደም ሲል በትግሉ ዘመን ለፖሊቲካዊ ዓላማዉና ለወታደራዊ ስልት(ስትራቴጂ) ጠቀሜታ ያወጣቸዉንና ተግባራዊ ያደረጋቸዉን አሠራሮች የመንግሥት ሥልጣን ከያዘ በኋላ እንኳን ብሔራዊ (ሃገራዊ) ፍላጎትን ሊይዝ በሚችል መልክ ተገቢዉን ማስተካከያ ማድረግ አለመቻሉና ያንኑ አሠራር አሁንም እንዲቀጥል ማድረጉ ነዉ። ይህ ሁኔታም ከዚህ በታች እንደተመለከተዉ በግልፅ ይታያል።

ለህወሀት የትጥቅ ትግል መሳካት ወደውጭ መውጫና መግቢያ በር አስፈላጊነትና የወልቃይት እስትራተጂአዊ ጠቀሚታ እጅግ የተቀራኙ ናቸው። ህወሀት ከደርግ ጋር የመሳሪያ ትግል ያደርግ በነበረበት ወቅት ለትጥቅ ትግሉ አስፈላጊ የሆነውን አቅርቦት ለማሳክት (ቁጥሩ እየጨመረ ለሚሄደውን ሰራዊት መሳሪያ፣ መድሀኒትን የህክምና እቃ፣ ምግብ ልብስ ወዘተ) በሀገር ውስጥ ከሚያገኘው አቅርቦት በቂ እንደማይሆን በመገንዘብ በዋናነት ከውጭ የሚገኝ እርዳታ ወሳኝ እንደሆነ ያውቅ ነበር። ይህን እርዳታም በበቂ ደረጃ ለማስገባት በድብቅና በተንጠባጠበ መልክ ሳይሆን ሰፋ ባለ መልኩ ለማድረግ በግድ ወደውጭ ሀገር በድንበር መገናኘትን የግድ ይል ነበር። ለዚህ ደግሞ በዋናናት አማራጭ ሆኖ የተገኘው ከሱዳን ጋር የሚያዋስነው የሀገራችን ግዛት በወቅቱ በጎንደር ክፍለ ሀገር ስር የነበረው የወልቃይት ጠገዴ ክፍል ነበር።በትግራይ ሰሜን በኩል የነበረው ኤርትራን ሻአቢያ የተቆጣጠረው ስለነበርናይህም ረዥሙ ሲታይ አስተማማኝነቱ አጠራጣሬ ስለሆነ በትግራይ ምስራቅ በኩል ያለው ደግሞ ባህር ጠርዝ ሲደርስ የሚቀም ሲሆን እንደልብ ለመውጣትና ለመግባት ደግሞ ከሚኖረው ጠቀሜታ አንጻር ታይ ዝቅተኛ ከመሆኑ የተነሳ ሕወሀት ከሱዳን ጋር የሚያገናኘውን ግዛት በራሱ ሙሉ ቁጥጥር ስር ማዋልን እጅግ ትኩረት ሰጥቶት ይንቀሳቀሰበት የነበረ ጉዳይ ነበር። ገና ከጅምሩ የወሰዳቸው እርምጃወችም ይህንኑ የሚያመለክቱ ናቸው።

ህወሀት ወደ የወልቃይት ጠገዴ ለመጀመሪያ ጊዜ ዘመቻ ባደረገበት ሰአት በትግራይ ውስጥ የነበረው ወታደራቂ ቁጥጥር ሰፊ አልነበረም። ወታደረዊ ሀይሉም እጅግ የዳበረ አልነበረም። ይህ በሆነበት ሁኔታ ነው ህወሀት ኢህአፓን ካሲምባ በመሳሪያ ሀይል ባስወጣው ባጭር ጊዜ ውስጥ እግር በእግር ተከታትሎ ከወልቃይት እንዲወጣ በማድረግ እስከ ሱዳን የሚወስደውን መስመር የተቆጣጠረው።

የህወሀት ወልቃይት ጠገዴን የመቆጣጠር ወታደራዊ እስትራተጂው በአውሮፓውአን አቆጣጠር በ1984፣ 85 በነበረው ድርቅ ጊዜ የተጫወተውን ታላቅ ጠቀሚታና፣ ህዝብን ወደሱዳን እንደፈለጉት ለማስወጣትና በሱዳን በኩልም በቀጥታ አስፈላጊውን ሁሉ ይቆጣጠረው ወደነበረው ቦታ ለማስገባት መሳሪያ መድሀኒት ምግብ፣ የውጭ ጋዜጠኞች የፖለቲካ ሰወች እንደልብ እንዲገቡና እነዲወጡ ማስቻሉ ወዘተ በቂ ምስክር ነው።

ይህ ባንድ በኩል ለወታደራዊ እስትራተጂ "በሌላ በኩል ደግሞ ወልቃይት በታሪክ የትገራይ ነው" በሚል አስተሳሰብ በቁጥሩ ያዋለው ክልልን በድህረ ደርግም ባወጣው የክልል አሸናሸን በዛው እንዲቀጥል ስለሆነ ባካባቢው ህዝብ በኩል ተቃዎሞና በማናነቱ ላይ ያተኮረ መራራ ትግል እነዲቀሰቀስ አድርጓል።
http://siteresources.worldbank.org/EXTSOCIALDEVELOPMENT/Resources/Ethiopia.pdf

ሕወሀት ኢህአዴግና አጋሮቹ በፈለጉት መልክ በሸነሸኑት ክልል ውስጥ የሚኖረው ህዝብ ስርአቱ የሚያካሂድበትን ሁለንተናዊ የመብት ረገጣ በመቃወም መብቱን ለማስረከብ የሚያካሂደው ትግል በሰፊው የተመዘገበ ሲሆን ከዚህም ውስጥ የወልቃይት ጠገዴ ነዋሪዎች፣ የኮንሶ ነዋሪዎች ወዘተ ተጋድሎዎች የሚጠቀሱ ናቸው። በዚህ አኳያ በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጉባኤ 141ኛ ልዩ ሪፖርት ያቀረበውን ሰፊ ጥናት ለመረጃነት መመልከት ያስፈልጋል።
https://ahrethio.org/wp-content/uploads/2016/07/HRCO-141st-Special-Report-English.pdf

የወልቃይት ጠገዴ ህዝብ ቀደም ባሉት ስርአቶች ከተለያዩ የኢትዮጵያ ግዛቶች የሚመጡ ዜጎች የተለያየ የስራ እድል የሚያገኙበት፣ ሀብትና ንብረት የሚያፈሩበት አልፎ ተርፎም ቋሚ መኖሪያቸው አድርገው የሚኖሩበት እንዲሁም ዘመናዊ ሰፋፊ የእርሻ ስራ በሰፊው ሲካሄድበት የቆየ ነው።

ይህ ሁሉ ሲሆን አካባቢው ለተወሰነ ብሄር ንብረት ተደርጎ ተከልሎ ለሌሎች የተከለከለበት ወይም የተወሰነ ብሄር ተወላጆች ጥቅም የተከለከለበት ሳይሆን ለሁሉም ኢትዮጵያዊ ክፍት የነበረበትን ሁኔታ ይታይ ነበር። ህወሀት ኢህአዴግ ተግበራዊ ያደረገው ብሄር ተኮር የአስተዳደር ክልል አሸናሸን ግን ባካባቢው ህዝብ የማናነት ጥያቄም ሆነባካባቢው መሬት ባለቤት ላይ ፣ በተለያ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን ግንኙነት ላይ ወዘተ አላስፈላጊ የሆነ ፣ ውጥረትንና ግጭትን ጋብዟል። በሌሎች ቦታወች እንደታየው ሁሉ ህወሀት/ኢህአዴግና አጋሮቹ የህዝብን ታሪክ፣ ያአስተዳደር አመችነትን የህዝብን ትስስር ወዘተ ሳያጤኑ እንደፈለጉ የሸነሸኑት አስተዳደር እነሆ ታላቅ ጥላን አጥልቶና ከፍተኛግጭትንም ቀስቅሶ ይገኛል ።

**ሸንጎ አባል ድርጅቶች /ግለሰቦች አመለካከት**

- የሸንጎ አባል ድርጅቶች /ግለሰቦች ከላይ በተነሱት ጉዳዮች ላይ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?
- ያመለካከት አንድነትና ልዩነቶቹ ምንድን ናቸው

**የሸንጎው አቋም ምን መሆን ይገባዋል።ማጠቃለያና የውሳኔ ሀሳብ**

- ሀገራችንን በብሄር ተኮር ክልል ለመሸንሸን የተወሰነውና ተግባራዊ የተደረገው ህዝብን ባሳተፈ፣ የተለያዩ አመለካከት ያላቸው ባለድርሻዎች ድምጽ በተካተተበትና በዴሞክራሲያዊ መንገድ የህዝብን ይሁንታ አግኝቶ በተመረጠ የህዝብ ተወካዮች የጸደቀ ሳይሆን ኢህአዴግና አጋሮቹ ለብቻቸው በፈጠሩትና በሚቆጣጠሩት ምክር ቤት የወሰኑት ስለሆነ ሸንጎ ይቃወማል።

- የተሸንሸኑት ክልሎች የህዝብን ታሪክ፣ ለአስተዳደር የሚኖርን አመችነት ፣በተለያዩ የሀገሪቱ ክልሎች ነዋሪ በሆነው ህዝብ መሀል ተመጣጣኝ እድገትን ለማስገኘት በሚረዳ ሁኔታ ክልሎች ተመጣጣኝ እድልን እንዲያገኙ ለማስቻል የሚያስችል መመዘኛ ወዘተ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሳይሆን በወቅቱ የፖለቲካ ስልጣኑን የጨበጡትን ክፍሎች (የህወሀት/ኢህአዴግንና አጋሮቻቸው ) የፖለቲካ፣ ወታደራዊና ወዘተ አላማ ለማሟላት የተደረገ ውሳኔ ስለሆነ ሸንጎው ይቃወማል።

- ህወሀት/ኢህአዴግና አጋሮቹ ብሄር ተኮር በሆነ መልክ የፈጠሯቸው ክልሎች እኛና እነሱ የሚል አመለካከትን የሚያበረታታ የሀገሪቱንና የህዝቡን አንድነት የሚያዳክምና ግጭቶችንም የፈጠረና እየተባባሱ እንዲሄዱ የሚያደርግ ስለሆነ ሸንጎ ይቃወማል።

- የተሸነሸኑት ክልሎች  በየክልሉ ውስጥ የሚገኙትን ማህበረሰቦች እኩልነት የሚያረጋግጡ ሳይሆን በተለያየ ቦታ ማህበራዊ ፍትህን ባዛባ ሁኔታ እኩልነትን ሳይሆን የበላይና የበታችነትን የሚፈጥርና ተግባራዊ የሚያደርግ ስለሆነ  ባንዳንድ ቦታወችም የተለያዩ ማህበረሰቦችን ማንነት በሚያዳክም ሁኔታ የሚካሄድ በመሆኑ ሸንጎ አጥብቆ ይቃወመዋል።

- ህዝብ በስርአቱየተነሳበማንነቱ  የሚደርስበትን በደል፣በመቃወም  የማህበራዊ ፍትህ መጥፋትን የመሬት ነጠቃን ፤መፈናቀልና አድልኦን  ወዘተ በመቃወም የሚያካሂደውን ትግል (ለምሳሌም በኦሮሚያ ፣ በወልቃይትና ጠገዴ፣ በጋምቤላ ወዘተ) ሸንጎ ይደግፋል፣ ለሙብት መከበር በሚያደርገው ትግል ከጎናቸው እንደሚቆምም ያረጋግጣል።

- ሸንጎ ህወሀት/ኢህአዴግ ኢትዮጵያውያንን በክልል ሸንሽኖ ከተወሰነ አካባቢ ጋር ብቻ የተሳሰሩ ለማድረግ "በብሄር ወጥ" የሆነ ክልሎችን ለመፍጠር የሚያደርገው እንቅስቃሴ የሀገራችንን ህዝብ ብዙህዊነት እጅግ ያላገናዘበና ግጭትን የሚጋብዝ ሰለሆነ አይቀበለውም ። ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የሀገሪቱ ክፍል የመኖር ሙብት እንዳለው ማወቅና ይህንንም ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል ብሎ ያምናል።

- በአንዳንድ ቦታወች ህወሀት ኢህአዴግ ለራሱ ፖለቲካዊ ስትራተጂ ሲል በሸነሸነው ክልሎች የጎሳ ስብጥርን ሙሉ በሙሉ በሚቀይር ሁኔታ የሚያካሂደው ሰፈራ እጅግ አደገኛ የሆነ አካሄድ ብቻ ሳይሆን በወገኖቻችንም መሀል አላስፈላጊ ቅራኔንና ግጭትን የሚጋብዝ ስለሆነ ሸንጎው የዚህ አይነቱ ተግባር ባስቸኳይ እንዲቆም  ያሳስባል።

- ያስተዳደር ክልሎች በብሄር ተኮር እንዲሸነሸኑ መሆናቸው  በህዝባችንና በሀገራችን አንድነት ላይ እጅግ ሰፊ ችግርንና ታላቅ አደጋን አጥልቷል። በዚህ ፖሊሲ ምክንያት እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን ተፈናቅለዋል፣ ንብረታቸው ተነጥቋል፣ ሕይወታቸው ጠፍቷል። ይህ ከቀጠለ እጅግ ሰፊ የእርስበርስ ግጭት የሚጋብዝእንደሆነ ሸንጎ ይገነዘባል ይህን ዓይነቱን ፖሊሲና ተግባርም ይቃወማል።

- የተዋቀሩት ክልሎች በፌደራሊዝምና ራስን በራስ ማስተዳደር ስም የሚንቀሳቀሱ ቢሆንም በተግባር የሚታየው ግን ክልሎች የፖለቲካ ነጻነት የሌላቸው ሲሆን የሚተዳደሩትም  በማከላዊነት በተሰየመው በህወሀት/ኢህአዴግና በአጋር ድርጅቶቹ ገዥነት መሆኑን ሸንጎ ይገነዘባል።

- መሬት የብሄር ብሄረሰቦች ነው በሚለው ፍልስፍናው ባንድ አካባቢ የሚኖር ዜጋ ከአካባቢው ውጭ የሚኖረውን ሙብትየተሸራረፈ ባይተዋርና ዝቅ ያለ አድርጓል። ይህ መሬትን የክልል የሚያደርገው አመለካከት የክልልን ድንበር ለማስፋፋት አንዱ ትልቅ የግጭት መንስኤ ሆኗል። በወልቃይትና ጠገዴ፣ በኦሮሚያና በሶማሌ፣ በአፋርና ሶማሊያ በጉጂና ቦረና፣ በአማራና ትግራይ፣ በኮንሶ፣  ወዘተ የሚታዩትን በምሳሌነት መመልከት ይቻላል።

- ለዚህና ለሌሎችም እጅግ ዘግናኝ ግፍ መሰረቱ የህወሀት/ኢህአዴግ አግላይና አምባገነን ስርአት በመሆኑ መሰረታዊ የስርአት ለውጥ በማምጣትም በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቀሱትንም ሆነ ሌሎች ችግሮች በብሄራዊ መግባባት፣ በሰጥቶ መቀበልና ፍትህዊ በሆነ መንገድ የህዝብንና የሀገርን እንድነት በሚያጠናክር ሁኔታ ለመፍታት ሸንጎው ባስቀመጣቸው መለስተኛ መግባቢያ ነጥቦች ዙሪያ ለስርአት ለውጥ የሚታገል ሰፊ የተቃዋሚ ህብረትና  የህዝብን ትግል ማፋፋም እንደሚገባ በድጋሚ አጽንኦት ሰጥቶ መታገል አስፈላጊ ነው።